በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበ□ል::

- □□ቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤
    - የኦቶና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመደበኛ በጀት ባንክ ሂሣብ (1000168506507) የማኑዋል የባንክ ሌጀር የሰኔ 30/2009 መጨረሻ በባንክ ያለ ቀሪ ጥሬ ገንዘብ መጠን ብር 19,948.41 የሚያሳይ ሲሆን የሰኔ 30/2009 የባንክ ሚዛን መግለጫ (Bank Statement) ብር 0.00 ሆኖ እያለ የሰኔ/2009 ባንክ ማስታረቂያ ግን በሁለቱም የሚገኘው (በሌጀር እና በባንክ) ያለ ቀሪ ሚዛን 0.00 እንደሆነ ተደርጎ ማስታረቂያው ተሰርቶ የቀረበ መሆኑ፤
    - የህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሂሳብ ምዝገባው ማንዋል በመሆኑ የመደበኛ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ምንም አይነት የሌጀር ምዝገባ የተከናወነ ባለመሆኑ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በውስጥ ኦዲት በጥሬ ገንዘብም ሆነ በሰነድ በሳጥን ተገኝቶ የተቆጠረ እንደሌለ የተገለጸ ቢሆንም ቆጠራው ከሌጀር ሚዛን ጋር የተመሳከረ ባለመሆኑ እና በሂሳብ ሪፖርቱም ላይ የሚታይ ሂሳብ ባለመኖሩ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፤
2. ለትምህርት ወደ ውጭ ሃገር ለተላኩ ሠራተኞች ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባው ሙሉ ደመወዛቸው በመከፈሉ በድምሩ ብር 163,200.00 ከመመሪያ ውጭ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
3. የፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ ለተለያዩ የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞች በድምሩ ብር 351,378.35 የትርፍ ሰአት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

4. መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ላዘጋጁ 34 የኮሚቴ አባላት ለእያንዳንዳቸው ብር 10,000.00 በድምሩ ብር 340,000.00፤ በንብረት ቆጠራ ለተሳተፉ 21 የኮሚቴ አባላት ለእያንዳንዳቸው ብር 5,000.00 በድምሩ ብር 105,000.00 እና የአምስት አመት ስትራቴጂክ ፕላን ላዘጋጁ ለ27 ኮሚቴ አባላት እንደ ደረጃቸው ከብር 30,000.00 እስከ ብር 1,000.00 በድምሩ ብር 149,000.00 በጠቅላላው ብር 594,000.00 በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ውሣኔ የተከፈለ መሆኑ፤
5. በዋናው ግቢ ያለውድድር በቀጥታ የብር 593,380.11 ዕቃ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤
6. በጨረታ መፈጸም የነበረበት ግዥ በዋናው ግቢ ብር 977,951.43 እና በኦቶና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 2,133,049.45 በድምሩ የብር 3,111,000.88 የዕቃና የአገልግሎት ግዢ በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ መሆኑ፤
7. ለሩዝ ግዢ መከፈል ከነበረበት ዋጋ በላይ ብር 12,000.00 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
8. በቀን 04/07/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 242116 በሂሳብ መደብ 6232 ብር 70,742.00 ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ለተከፈለ ክፍያ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳያቀርብ ሂሣቡ የተወራረደ መሆኑ፣
9. ለመድሃኒት ግዥ ለመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የተከፈለው ብር 295,617.67 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራርደ መሆኑ፤
10. በዋናው ግቢ በ2008 በጀት ዓመት የተፈፀሙ የብር 12,682,431.42 የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች በበጀት እጥረት ምክንያት ሳይከፈል የቀረ በማለት በ2009 በጀት ዓመት ተከፍሎ የተመዘገበ መሆኑ፤
11. በድምሩ ብር 34,470,720.73 በትክክለኛው የወጪ ሂሳብ መደብ (አርዕስት) ያልተመዘገበ መሆኑ፣
12. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል ለሚገዙ ሶስት አምቡላንሶች መግዣ በቅድሚያ የተከፈለው ብር 2,981,647.08 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲኖርበት በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤
13. በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ብር 9,676,303.39 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤
14. ለዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 1,543,667.59 እና ከካፒታል በጀት ብር 75,832,857.27 በድምሩ ብር 77,376,524.86 ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

1. በዩኒቨርሲቲው በመከናወን ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ኦዲት ሲደረግ በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ የሚገኙ 11 ፕሮጀክቶች የሚገኙ መሆኑ፤

2. የግንባታ ሥራዎች 80% ሲሆናቸው የሥራ ተቋራጮች የወሰዱትን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ በሙሉ መመለስ ሲኖርባቸው ከ7 (ሰባት) ሥራ ተቋራጮች በድምሩ ብር 2,283,138.16 የግንባታ ቅድሚያ ክፍያ በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ እና በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፤

1. ለዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 9,668,573.42 እና ከካፒታል በጀት ብር 71,661,398.63 በድምሩ ብር 81,329,972.05 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) መሆኑ፤
2. የዩኒቨርሲቲው የንብረት አጠባበቅና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፤

   የአላቂ እና የቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝ፣

   የዋናው ግቢ፣

   - ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት ከትምህርት ሚኒስቴር በእርዳታ የገቡ በርካታ ዘመናዊ የምግብ ማብሰያ እቃዎች አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆኑ፤
   - የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ መዝገቦች ከወጪ.ቀሪ ጋር ያልተገናዘበ መሆኑ፤
   - በቆጠራ ወቅት ብዛት ያላቸው አላቂ የሆኑ የግንባታ ዕቃዎች፣ የቢሮ ዕቃዎችና የትምህርት መሳሪያዎች ዋጋቸው ያልተገለጸ መሆኑ፤
   - የቋሚ ዕቃ እና የአላቂ ዕቃ መጋዘን ጠባቂዎች በአዳዲስ ሰራተኞች ሲተኩ ርክክብ የተካሄደ ቢሆንም በውስጥ ኦዲት ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ፤
   - በአላቂ ንብረት መጋዘን ንብረት የመያዝና የገቢና ወጪ ምዝገባ ሥራዎች በአንድ ሰራተኛ እየተከናወነ የሚገኝ መሆኑ፤
   - በዋናው ግቢ በርከት ያሉ አሮጌ ጎማዎች፣ የመኪና ባትሪ፣ ብላክ ቦርዶች፣ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፣ ሎከሮች፣ ፍራሾች፣ ትራሶች፣ ቆርቆሮዎች፣ የቀለም ቆርቆሮዎች፣ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ማይክሮስኮፖች፣ የኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያዎች፣

ቴሌቪዥኖች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖችና ስፒከሮች እንዲሁም ወንበርና ጠረጴዛዎች ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ የተቀመጡ መሆኑ፤

- በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የተማሪዎች መኖሪያ ህንጻ፣ የመማሪያ ህንጻና የአስተዳደር ቢሮዎች እንደ ቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ አለመመዝገባቸው፤

የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ፣

- ቋሚ፣ አላቂ እና አሮጌ እቃዎች ከንብረት ክፍል ጥበት የተነሳ በአንድ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የቋሚ፣ አላቂ እና ተመላሽ እቃዎች በአንድ ሰራተኛ ንብረት የመያዝ፤ ገቢ እና ወጪ የማድረግ ስራ የሚከናወን መሆኑ፤
- በንብረት ክፍል ውስጥ ቢን ካርድ ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- የቋሚ ዕቃና የስቶክ መዛግብት ምዝገባ ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የንብረት ተጠቃሚ ሰራተኞች ካርድ (user card) ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- የንብረት ቆጠራ ስለመከናወኑ የሚገልጽ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- ለተማሪዎች ወርሃዊ፣ ሳምንታዊና ዕለታዊ የምግብ ግብዓት ከዋናው ግቢ የሚመጣ ቢሆንም ሞዴሎችና ቢንካርድ ሥራ ላይ ባለመዋሉ ገቢና ወጪ የሚከናወነው በደብዳቤ መሆኑ፣

3. የዩኒቨርሲቲው የመድሃኒት አጠባበቅና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፤
    - ከሆስፒታሉ የመድሃኒት መጋዘን ወደ ተለያዩ አገልግሎት መስጫ እና ማደያ ክፍሎች ከመሰራጨቱ በፊት ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ የመድሃኒትና ህክምና ኮሚቴ ለየከፍሎቹ በሚያዘጋጀው መዘርዝር መሰረት አለመሆኑ እና ይህ አሰራር በሆስፒታሉ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
    - በሆስፒታሉ በዋናው የመድኃኒት መጋዘን ውስጥ በአንድ ሰራተኛ ንብረት የመያዝ፣ ገቢ እና ወጪ የማድረግ ስራ እንደሚከናወን እንዲሁም ቢን ካርድ፣ ስቶክ ካርድና ሞዴሎች ወቅታዊ ምዝገባ ያልተደረገ መሆኑ፤
    - የህክምና ቋሚ ዕቃ መጋዘን ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ የሌላቸው ሲሆን እቃዎችም በአግባቡ ያልተቀመጡ መሆኑ፤
    - የመድኃኒት ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መጋዘን በአንድ ሰራተኛ ንብረት የመያዝ፤ ገቢ እና ወጪ የማድረግ ስራ እንደሚከናወንና ወቅታዊ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፤
    - መድሃኒት ለተጠቃሚው መሸጥ ያለበት ከ20% ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ መሆን ሲገባው ሆስፒታሉ 30% የትርፍ ምጣኔ በማድረግ መድሃኒት ለተጠቃሚው ከመሸጡ ባሻገር የመድሃኒቶቹ ዋጋም በዝርዝርና በሚታይ መልኩ ለተጠቃሚው ያልተለጠፈ መሆኑ፣

- ሆስፒታሉ የመድሃኒት ቆጠራ በሚያደርግበት ወቅት በቆጠራው ኮሚቴ ውስጥ የውስጥ ኦዲት በመሪነት መሳተፍ ቢኖርበትም በግቢው ያልተደረገ መሆኑ፤ የቆጠራው ውጤት ከመድሃኒት መቆጣጠሪያ መዝገቦች ከወጪቀሪ ጋር የማገናዘብ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣ እንዲሁም በስቶክና ቢን ካርድ ቆጠራ ስለመከናወኑ ማስረጃ የሚሆን ነገር አለመገኘቱ፤
- በሆስፒታሉ የመደኃኒት አቅርቦት፣ ክምችት፣ አያያዝ፣ አመዘጋገብ፣ ስርጭት፣ ሽያጭ እና አወጋገድ በሚመለከት ኦዲት አለመከናወኑ፤
- በስድስቱም የማደያ ክፍሎች የመድሃኒት ክምችት እና እንቅስቃሴን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ፣ ስቶክ ካርድ ወይም ዘመናዊ ሶፍትዌር በመጠቀም ያልተቆራረጠ ወቅታዊ ምዝገባ የማይደረግ መሆኑ፤
- ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች እስኪወገዱ ተለይተው እንዲቀመጡ የሚደረግ ቢሆንም ሳይወገዱ መቀመጣቸው፤

4. የዩኒቨርሲቲው የተሽከርካሪዎች አጠባበቅና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፤
   - እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ፣
5. የዩኒቨርስቲው የውስጥ ኦዲት ክፍል የውስጥ ገቢ ሂሳብን ኦዲት እያደረገ ሪፖርት የማያቀርብ መሆኑ፤
6. በዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት 9 የኦዲት ባለሙያዎች የሚያስፈልጉ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 4 የኦዲት ባለሙያዎች ሲኖሩ ከዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይል መዋቅር ጋር ሲነፃፀር 5 የኦዲት ባለሙያዎች በቅጥር ያልተሟላ መሆኑ፤ በዚህም ምክንያት የ2ኛ ሩብ ዓመት ኦዲት ሪፖርት በወቅቱ ሳይቀርብ ከ3ኛ ሩብ ዓመት ኦዲት ሪፖርት ጋር የቀረበ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. **የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ፣**

1.1 **የባንክ ማስታረቂያ እና የሳጥን ሌጀር ሚዛን ምዝገባን ይመለከታል፣**

1.1.1 **ግኝት**

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 በፊደል (ሀ) የሂሳብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት መረጋገጥ እንዳለበትና በፊደል(መ) በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ላይ የሚታየው የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት መረጋገጥ እንደሚኖርበት ይገልጻል፡፡ እንዲሁም በዚሁ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/6 በፊደል (መ) በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጊዜያዊ ሂሳቦች መዝጊያ ምዝገባ ተከናውኖ የዘመኑን ሂሳብ በመዝጋት ቋሚ ሂሳቦች ለቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፍ እንዳለባቸው በሚገልፀው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- የኦቶና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመደበኛ በጀት ባንክ ሂሣብ (1000168506507) የማኑዋል የባንክ ሌጀር የሰኔ 30/2009 መጨረሻ በባንክ ያለ ቀሪ ጥሬ ገንዘብ መጠን ብር 19,948.41 የሚያሳይ ሲሆን የሰኔ 30/2009 የባንክ ሚዛን መግለጫ (Bank Statement) ብር 0.00 ሆኖ እያለ የሰኔ/2009 ባንክ ማስታረቂያ ግን በሁለቱም የሚገኘው (በሌጀር እና በባንክ) ያለ ቀሪ ሚዛን 0.00 እንደሆነ ተደርጎ ማስታረቂያው ተሰርቶ የቀረበ መሆኑ፤
- የህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሂሳብ ምዝገባው ማንዋል በመሆኑ የመደበኛ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ምንም አይነት የሌጀር ምዝገባ የተከናወነ ባለመሆኑ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በውስጥ ኦዲት በጥሬ ገንዘብም ሆነ በሰነድ በሳጥን ተገኝቶ የተቆጠረ እንደሌለ የተገለጸ ቢሆንም ቆጠራው ከሌጀር ሚዛን ጋር የተመሳከረ ባለመሆኑ እና በሂሳብ ሪፖርቱም ላይ የሚታይ ሂሳብ ባለመኖሩ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

1.1.2 **ስጋት** ፣

- የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን እንዲያሳዩ ባለመደረጉ የሂሳብ ሪፖርቶች የተቋሙን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በትክክል ላያሳዩ ይችላሉ፡፡
- ትክክለኛ የባንክ ማስታረቂያ ተሰርቶ አለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የማያስችል ከመሆኑም በላይ የመንግስት ገንዘብ ለምዝበራ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

- የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንቅስቃሴን በወቅቱ አለመመዝገብ ለመንግስት ገንዘብ ጉድለትና ብክነት ያጋልጣል፡፡

1.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

በጥሬ ገንዘብ ላይ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ፤ እንዲሁም በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይቀርብ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ እንዲሁም በኮሌጁ የሚገኙ እያንዳንዱ አካውንት በየወሩ ትክክለኛ የሂሳብ ማስታረቂያ ተሰርቶ ሊቀርብ ይገባል፡፡ የኮሌጁ የመደበኛም ሆነ የውስጥ ገቢ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንቅስቃሴ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) እንዲያዝ የስራ አመራሩ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

1.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

- ማኑዋል ሌጀርና የባንክ ስቴትመንት ተመሳሳይ አለመሆኑ ግኝቱ ትክክለኛ ስለሆነ ለወደፊቱ እናስተካክላለን፡፡
- የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሂሳብ ምዝገባ ቀደም ስል የባለሙያ እጥረት ስለነበረብን በማኑዋል እየተሠራ የቆየ ቢሆንም አሁን የIBEX ባለሙያ ስለተቀጠረ በIBEX ምዝገባ ጀምረናል፡፡

2. <u>የወጪ ሂሳብ</u>፣

2.1. <u>ደመወዝና ተዛማች ወጪዎች</u> ፣

2.1.1.1 <u>ግኝት፣ ለትምህርት ወደ ውጪ ሃገር ለሄዱ መምህራን የተከፈለ ደመወዝ፣</u>

ለትምህርት ወይም ሥልጠና በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር ተልከው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሠራተኞች ደመወዝ አከፋፈልን በተመለከተ እስከ አንድ ወር ለሚቆይ ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር ለሚሄዱ ሙሉ ደመወዛቸው እንዲከፈል ሆኖ ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ የሚሄዱት ግን ከተፈላጊ መረጃዎች ጋር ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ሲፈቀድ በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው እንደሚከፈላቸው ሚያዝያ 20/1990 በቁጥር 80-አጠ52/01/09 ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት መመሪያ መተላለፉ ተገልጾ መስከረም 22/1993 በቁጥር መ19/ጠ49/2/56 ከቀድሞው የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን መመሪያው የተላለፈ ቢሆንም፣

- በዩኒቨርሲቲው የሰው ሃብት አስተዳደር እና ልማት ዳይሬክቶሬት በቀረበው መረጃ መሰረት በዋናው ግቢ ለትምህርት በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር የተላኩ ሠራተኞች ሙሉ ደመወዛቸው በመከፈሉ በድምሩ ብር 163,200.00 ከመመሪያ ውጭ በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ተ.ቁ	የመምህሩ ስም	መምህሩ ወደ ውጭ ሃገር ለትምህርት የሄደበት ጊዜ	ሙሉ ደመወዝ ለመምህሩ የተከፈለበት ጊዜ	ደመወዝ	የተከፈለው	መከፈል የነበረበት	ልዩነት (በብልጫ የተከፈለ)
1	ሙደሲር ነስሩ	10/10/08	ከሀምሌ 01/2008-ሀዳር 30/2009	10,470.00	52,350.00	26,175.00	26,175.00
2	ሲሳይ በላይ	30/12/08	ከነሃሴ 01/2008-ሰኔ 30/2009	10,470.00	115,170.00	57,585.00	57,585.00
3	ኢዮብ ጩቃሶ	10/08/08	ከሃምሌ 01/2008-ሀዳር 30/2009	10,470.00	52,350.00	26,175.00	26,175.00
4	ይግረማቸው እሸቱ	05/11/08	ከነሃሴ 01/2008-ሀዳር 30/2009 30/2009	8,310.00	33,240.00	16,620.00	16,620.00
5	አበሻ ሽርኮ	18/01/09	ከጥቅምት 01/2009 እስከ ታህሳስ 30/09	10,470.00	31,410.00	15,705.00	15,705.00
6	ቴዎድሮስ ደረሰ	11/11/08	ከነሃሴ 01/08 እስከ ሀዳር 30/09	10,470.00	41,880.00	20,940.00	20,940.00
						ድምር	163,200.00

2.1.1.2 ስጋት፣

ከመመሪያ ውጭ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

2.1.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

ከመመሪያ ውጭ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም በደመወዝ ክፍያ ወቅት አስፈላጊው ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

2.1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በወቅቱ ወደ ውጭ ለትምህርት የሄዱ መምህራን ደመወዝ የተከፈለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ተከታትለን ማስመለስ የተጀመረ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.1.2.1 ግኝት፤ የአስተዳደር ሰራተኞች ትርፍ ሰዓት ክፍያ

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/ል/ት/ሚ/1/54/2/ በቀን 17/09/2002 ስለ ትርፍ ሰዓት ክፍያ አፈጻጸም በማስመልከት ከኤጀንሲዉ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 የተላለፈዉ የአፈጻጸም መመሪያ ተግባራዊ ሳይደረግ እንደቆየ ጠቅሶ መመሪያዉ በተለይም በሥራ ባህሪያቸዉ ምክንያት ከመደበኛ ሥራ ሰዓት ውጪም ጭምር ለሚሰሩ የመንግስት መ/ቤቶች ጠቃሚ እንደሚሆን ስለታመነበት

ያለአግባብ ብክነት እንዳይከሰት የተጠቃሚ መ/ቤቶች የሥራ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በኤጀንሲዉ በኩል በልዩ ሁኔታ እየተፈቀደ ሥራ ላይ እንዲውል አሳስቧል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- የፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ ለተለያዩ የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞች በድምሩ ብር 351,378.35 የትርፍ ሰአት ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 1** ቀርቧል፡፡

2.1.2.2. <u>ስጋት</u>

ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ካልተፈጸሙ የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል ፡፡

2.1.2.3. **<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>**

ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.2.4. **<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>**

በ2009 ዓ.ም በተከሰተው ወቅታዊ ሁኔታዎች በመነሳት የግቢውን ፀጥታና ደህንነት ለማስጠበቅ የመማርና ማስተማር ሥራ ዙሪያ ችግር እንዳይፈጠር በማኔጅመንት ተወስኖ ቢከፈልም በአሁኑ ሰዓት ለተፈቀደላቸው የሥራ ክፍሎች ብቻ መመሪያና ደንብ ተጠብቆ እየተከፈለ ይገኛል፤ የእርምት እርምጃ ተወስዷል፡፡

2.1.3.1 **<u>ግኝት፤ ለኮሚቴዎች አላግባብ የተከፈለ፤</u>**

የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 አንቀጽ 10 ተራ.ቁ 2 እና 6 የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት የሚረዳው ዋነኛው መሳሪያ መሆኑን በመገንዘብ ስርዓቱን የመቅረጽ፣ በስራ ላይ የመዋልና በሚፈለገው መንገድ እየተሰራበት ለመሆኑ የመከታታል እንዲሁም የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን በማስከበሩ ተግባር ላይ ሁሉም የመ/ቤቱ ሰራተኞች ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት የመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ ሃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በ04/13/08 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 239717 ብር 340,000.00 መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ላዘጋጁ 34 የኮሚቴ አባላት ለእያንዳንዳቸው ብር 10,000.00 እንዲሁም በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 239716 ብር 105,000.00 በንብረት ቆጠራ ለተሳተፉ 21 የኮሚቴ አባላት ለእያንዳንዳቸው ብር 5,000.00 በድምሩ ብር 445,000.00 የተከፈለ መሆኑ፤

- በ17/12/08 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 468473 የአምስት አመት ስትራቴጂክ ፕላን ላዘጋጁ ለ27 ኮሚቴ አባላት እንደ ደረጃቸው ከብር 30,000.00 እስከ ብር 1,000.00 በድምሩ ብር 149,000.00 የተከፈለ መሆኑ፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 594,000.00 ከመንግስት መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.1.3.2. ስጋት

ዩኒቨርስቲዉ መንግሥት ያወጣዉን ደንብና መመሪያ ተከትሎ የማይሰራ ከሆነ የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ ለብክነት እና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.1.3.3. የማሻሻያ ሃሳብ

አላግባብ ከመንግስት መመሪያ ዉጭ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- ዩኒቨርሲቲው ከጊዜ ወደ ጊዜ የአሠራር ሥርዓትን እያሻሻለ አዲስ ለሚከፈቱ የትምህርት ፕሮግራሞች አጋዥ የሆኑ የሠለጠነ የሰው ሀይል በአስተዳዳር ዘርፍ በማስፈለጉ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ጥናት ላደረጉ ባለሙያዎችና እና GTP(2) ለቀሪ ሶስት አመታት የተከለሰ እስትራቴጅክ እቅድ ላዘጋጁና ለረጅም ጊዜ ሳይቋረጥ ቋሚ የንብረት ቆጠራ ላካሄዱት ሠራተኞች ከሥራው አስፈላጊነት የተነሳ በማኔጅመንት ተወስኖ የተከፈለ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- ለስትራቴጂክ ፕላን ላዘጋጁት በማኔጅመንት በተወሰነው መሰረት ታይቶና መምህራንም ስለሆኑ ሙያዊ እገዛ በማድረግ ስለሰሩ የተከፈለ መሆኑን እገልጻለሁ፡፡

2.2 ለዕቃና አገልግሎት ግዥ፣

2.2.1.1 ግኝት፣ በቀጥታ የተገዛ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ፣

ሰኔ/2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- **በዋናው ግቢ** ከመመሪያው ውጭ ያለውድድር በቀጥታ የብር 593,380.11 ዕቃ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር በሰንጠረዡ ተመልክቷል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ	አቅራቢ ድርጅት	የእቃው ዓይነት	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	20/10/09	BPV 282945	ኤሊያስ አብድራህማን ሻፊ	የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች	6218	64,998.00
2	19/10/09	BPV 282936	አቃቂ የእንስሳት መኖ ማዳራጃ ኃ/የተ/የግ/ማ	የዶሮ መኖ	6223	77,400.00
3	19/10/09	JV 282940	ጌታሁን ያቆብ ኤሌክ. ሙባረክ ራህመቶ	የኤሌክትሪክ ዕቃዎች	6244	189,232.50
4	30/11/09	JV 284577	ዑቡንቱ ኮምፒዩተር ሶሉዩሽን	ለጥበቃ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች	6218	77,749.61
5	13/06/09	JV 282883	ዘካሪያስ ዳኜ ማተሚያ ቤት	የመጽሐፍት ሕትመት	6215	184,000.00
					ድምር	**593,380.11**

2.2.1.2 ስጋት ፤

ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብም ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.2.1.3 **የማሻሻያ ሃሳብ**፣

ግዢዎች በግዢ መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.2.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ**፣

ዩኒቨርስቲው ለ2009 በጀት ዓመት ለተማሪዎች ምረቃ አገልግሎት የሚውል እና የግንባታ ፕሮጀክት የጀኔሬተር ዕቃዎች በመበላሸትና አስቸኳይ ግዥ ስለሚያስፈልገው ከ5ቱ የግዥ ዘዴዎች በቶሎ የሚደርሰውን በመምረጥ ግዥ የፈጸምን ሲሆን ለቀጣይ ማሻሻያ እንወሰዳለን፡፡

2.2.2.1 **ግኝት፤ ተቆራርጦ በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸሙ ግዥዎች፤**

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 33/2 እና ሰኔ 2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀጽ 15/2 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ በአዋጁ አንቀጽ 33/4 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ አዋጁ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ሥርዓቶችን ለመሸሸ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን መከፋፈል እንደሌለባቸው እንዲሁም፣ በመመሪያው አንቀጽ 24/1 እና 24/4 መሠረት ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም

በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋቸው በመመሪያው በተጠቀሰው መሠረት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ ለመፈፀም እንደሚቻል የተገለጸ ቢሆንም፤ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- **በዋናው ግቢ** የዕቃና የአገልግሎት ግዥ በድምሩ ብር 977,951.43 (ዝርዝር ሁኔታው **በአባሪ ቁጥር 2** ተመልክቷል)፤
- **በኦቶና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ** በድምሩ ብር 2,133,049.45 የዕቃና የአገልግሎት ግዥ (ዝርዝር ሁኔታው **በአባሪ ቁጥር 3** ተመልክቷል)፤

በአጠቃላይ ድምር በጨረታ መፈጸም የነበረበት የብር **3,111,000.88** ግዥ በዋጋ ማወዳደሪያ ተገዝቶ ተገኝቷል፡፡

2.2.2.2 ስጋት

ግዥ በአዋጁና መመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥም ይችላል፡፡

2.2.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ግዢዎች በግዢ መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.2.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- ዩኒቨርስቲው ለ2009 በጀት ዓመት ለተማሪዎች ምረቃ አገልግሎት የሚውል፤ ከተማሪዎች ካፍተሪያ እና የግንባታ ፕሮጀክት የጀኔሬተር ዕቃዎች በመበላሸትና አስቸኳይ ግዥ ስለሚያስፈልገው ከ5ቱ የግዥ ዘዴዎች በቶሎ የሚደርሰውን በመምረጥ ግዥ የፈጸምን ሲሆን ለቀጣይ ማሻሻያ እንወሰዳለን፡፡
- በኦቶና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በድምር 2,133049.45 የዕቃ ግዥ ዋጋ ማወዳደሪያ ዘዴ ተገዝቷል፤ የዋጋ ማቅረቢያ ከግዥ ዜደዎች አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን በግልጽና በውስን የጨረታ ዘዴ ብንጠቀም የበለጠ የተሻለ መሆኑን እንረዳለን፡፡ የጤና ሳይንስ ህክምና ኮሌጅ ሥራ ከሁኔታዎች አስገዳጅነት የተነሳ የዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ በተወሰነ ተጠቅመናል ለወደፊት እናስተካክላለን፡፡

2.2.3.1 ግኝት፤ በብልጫ የተከፈለ የሩዝ ግዥ፤

በጀት ዓመት በማዕቀፍ በተፈጸመ የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ግዥ የውል ስምምነት በልዩ የውል ሁኔታ በአ.ው.ሁ ቁጥር 15.2 የዋጋ ማስተካከያ በፌዴራል የመንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ን.አ.16.14.4. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ በሚመለከት ከፊደል ሀ እስከ መ ተገልጿል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በቀን 08/03/09 በቁጥር 1-9-3/1104 በተላከው የዋጋ ዝርዝር መሰረት የሩዝ ዋጋ ከ12/02/09 ጀምሮ ብር 1,148.00 መሆኑ ተመልክቷል። በ26/02/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 241153 በተፈጸመ ግዥ በሞዴል 19 ቁጥር 56604 ብዛት 60 ኩንታል በቀን 14/02/09 የገባ ቢሆንም የሩዝ ዋጋ ብር 1,148.00 መሆን ሲገባው ቀድሞ በነበረው ዋጋ ብር 1,348.00 ግዥ በመፈጸሙ በብልጫ ብር 12,000.00 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

2.2.3.2 <u>ስጋት</u>

ግዢዎች በውሉ መሰረት ተፈጻሚ ካልተደረጉ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ይዳርጋል።

2.2.3.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በቀን 08/03/09 በቁጥር 1-9-3/-1104 ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በተላከው የዋጋ ዝርዝር መሰረት በብልጫ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል ።

2.2.3.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

ለድርጅቱ የክፍያ ደብዳቤ የተዘጋጀው በ19/02/2009 ሲሆን ከእስታስቲክስ ኤጀንሲ ደብዳቤው የመጣው በ08/03/2009 በመሆኑ ክፍያው ቀድሞ የተከፈለ መሆኑን እንገልጻለን።

2.2.3.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

ክፍያው የዋጋ ማስተካከያው ደብዳቤ ከመድረሱ በፊት የተፈጸመ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው ለአቅራቢው ደብዳቤ በመጻፍ በብልጫ የተከፈለውን ገንዘብ ማስመለስ ይኖርበታል።

2.2.4.1 <u>ግኝት፣ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የቀረበለት እና ማስረጃ ያልቀረበለት ክፍያ፣</u>

በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 7 የተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጂናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት የታዘዘ ሲሆን በመመሪያው ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 7 ደግሞ ክፍያ ለሚፈጸምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረቡ እንዲሁም ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ሥልጣን ባለው አካል መፈቀዱ መረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል። በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ፣

- በቀን 04/07/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 242116 በሂሳብ መደብ 6232 ብር 70,742.00 ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ለተከፈለ ክፍያ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳያቀርብ ሂሣቡ የተወራረደ መሆኑ፣

- በቀን 18/08/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 284928 ብር 295,617.67 ከመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የመድሃኒት ግዥ ሲፈፅም በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራርደ መሆኑ፤ በኦዲቱ ታውቋል።

2.2.2.2 ስጋት ፣

የወጪ ሂሳብ ህጋዊ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተመዝግቦ ሪፖርት መደረጉ የመንግሥትን ገንዘብ ለብክነት ይዳርጋል፣ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

2.2.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

ለሂሳቦቹ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ሆኖ ለወደፊቱ ክፍያዎች ከመወራረዳቸው በፊት የተሟላና ህጋዊ ደጋፊ ማስረጃ መቅረቡን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

2.2.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደውን በሚመለከት በተሰጠ ምላሽ ከኢትዮጵያ መድኃኒት ፈንድ ደረሰኙን በማቅረብ እናያይዛለን፡፡
- ደረሰኝ ያልቀረበለትን በሚመለከት በተሰጠ ምላሽ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በማምጣት እናያይዛለን፡፡

2.2.5.1 ግኝት፣ በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ፣

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስከጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪዉን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪዉ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ወስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚሁ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በ2008 በጀት ዓመት **በዋናው ግቢ** የተፈፀሙ የብር 12,682,431.42 የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች በበጀት እጥረት ምክንያት ሳይከፈል የቀረ በማለት በ2009 በጀት ዓመት ተከፍሎ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ በሰንጠረዡ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የሂሳብ መደብ	የገንዘቡ መጠን
1	01/13/08	239788	ለኢንጅነሪንግ ላብራቶሪ አገልግት የሚውሉ እቃዎች ግዥ	6314	839,552.21
2	27/02/09	239851	ለአይሲቲ ዕቃዎች ግዥ	6314	2,035,623.67
3	28/02/09	239870	ለኢንጅነሪንግ ላብራቶሪ አገልግት የሚውሉ እቃዎች ግዥ	6314	2,244,551.60
4	25/05/09	241911	ለጤፍ ማስፈጪት አገልግሎት የተከፈለ	6216	375,830.00
5	08/03/09	239847	ለላውንደሪ ሳሙናና ዲተርጀንት ግዥ	6218	377,713.82
6	21/11/08	937874	ለቀን ሰራተኞች የሰኔ ወር 2008 ዓ/ም ምንዳ ክፍያ	6114	103,760.00

7	30/12/08	239932	ለሸሚዝ ግዥ	6211	326,876.00
8	11/12/08	239767	ለተመሪዎች ዶርም አገልግት የሚውል ሎከር ግዥ	6314	2,345,655.00
9	11/12/08	239766	ለኢንጅነሪንግ ላብራቶሪ አገልግት የሚውሉ እቃዎች ግዥ	6314	3,165,820.87
10	16/12/08	239606	ለሰራተኞች ደንብ ልብስ ግዥ	6211	168,998.25
11	18/12/08	239778	ለፓወር ኬብል ግዥ	6324	698,050.00
				ድምር	**12,682,431.42**

2.2.5.2 <u>ስጋት</u>፣

ክፍያዎች በጀት ዓመታቸውን ጠብቀው የማይፈፀሙ እና የማይመዘገቡ ከሆነ የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታውን ካለማሳየቱም በተጨማሪ በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

2.2.5.3 **<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>** ፣

ዩኒቨርሲቲው በጀት የሚመደብለት በየበጀት አመቱ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ስለሆነ ለወደፊቱ ሊስተካከል ይገባል፡፡

2.2.5.4 **<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>**፣

በበጀት ዓመት ከተማሪዎች ግብዓት አቅርቦትና ሌሎች ግብዓቶችን ለዩኒቨርስቲው አቅርበው በወቅቱ የጥሬ ገንዘብ እጥረት ምክንያት ለአቅራቢዎች ባለመከፈሉ የዩኒቨርስቲው ማኔጅመንት ኮሚቴ በቁጥር ወሶዩ47/04/26 በቀን 11/12/08 በተ.ቁ 2 መሰረት በ2009 በጀት ዓመት እንዲከፈል በተወሰነው ውሳኔ መሰረት የተከፈለ መሆኑን እየገለጽን ለወደፊቱ ጥንቃቄ የሚደረግ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.2.6.1 **<u>ግኝት፤ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ፤</u>**

የወጪ ሂሳቦች ነሃሴ 1999 በወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ (Chart of Accounts) መሠረት መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በዋናው ግቢ

- በሂሳብ መደብ 6212 መመዝገብ የነበረበት ብር 1,141,605.00 በ6271፣
- በሂሳብ መደብ 6322 መመዝገብ የነበረበት ብር 12,184,872.41 6323፣
- በሂሳብ መደብ 6322 መመዝገብ የነበረበት ብር 13,754,451.65 በ6323፣
- በሂሳብ መደብ 6322 መመዝገብ የነበረበት ብር 2,436,074.47 በ6323፣
- በሂሳብ መደብ 6315 መመዝገብ የነበረበት ብር 189,000.00 በ6223፣
- በሂሳብ መደብ 6313 መመዝገብ የነበረበት ብር 632,500.00 በ6243፣
- በሂሳብ መደብ 6313 መመዝገብ የነበረበት ብር 698,349.00 በ6314፣
- በሂሳብ መደብ 6313 መመዝገብ የነበረበት ብር 5,199,725.00 በ6314፣

- በሂሳብ መደብ 6323 መመዝገብ የነበረበት ብር 182,735.00 በ6324፣
- በሂሳብ መደብ 6313 መመዝገብ የነበረበት ብር 918,755.70 በ6324፣
- በሂሳብ መደብ 6323 መመዝገብ የነበረበት ብር 132,652.50 በ6223፣

በድምሩ ብር 37,470,720.73 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.2.6.2 ስጋት

ወጪዎች በትክክለኛው የሂሳብ መደባቸው የማይያዙ ከሆነ የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታውን ካለማሳየቱም በተጨማሪ በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

2.2.6.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ዩኒቨርሲቲው በጀት የሚመደብለት በየወጪ ሂሳብ ርዕሱ ተለይቶ ስለሆነ የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ክፍያ መፈፀሙ መመሪያን የጣሰ ከመሆኑም በላይ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ምክንያት ስለሚሆን ለወደፊቱ ሊስተካከል ይገባል፡፡

2.2.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለናል፤ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እናደርጋለን፡፡

2.2.7.1 ግኝት፤ በወጪ የተመዘገበ ቅድመ ክፍያ፣

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ስለወጪ ሂሳብ አያያዝ በንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ለ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም ግን፤

- በ2/12/08 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 239770 ብር 2,100,000.00 እና በ13/04/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 241851 ብር 881,647.08 በድምሩ ብር 2,981,647.08 በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል ለሚገዙ ሶስት አምቡላንሶች መግዣ በቅድሚያ የተከፈለ ሲሆን ሂሳቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲኖርበት በወጪ የተመዘገበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2.7.2 ስጋት ፣

ዩኒቨርሲቲው ላወጣው ወጪ እቃውን ወይም አገልግሎቱን ማግኘቱን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

2.2.7.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

የወጪ ሂሳብ በሚመዘግብበት ወቅት ለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም አላግባብ በወጪ ለተመዘገበው ሂሣብ ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግ ይገባል፡፡

2.2.7.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

የማስተካከያ ምዝገባ በማድረግ የምናርም ስለሆነ በተሰብሳቢነት እንዲያዝ እርምት ይወሰድበታል፡፡

2.3 <u>የግንባታ ሂሳብ</u>

2.3.1.1 <u>ግኝት፤ ያልተጠናቀቁ የግንባታ ሥራዎች፤</u>

የፌዴራል መንግስት የግዢ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 28 ንዑስ ቁጥር 1 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የተለያዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ከአቅራቢዎች (ከስራ ተቋራጮች) ጋር የተደረገውን የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት በዩኒቨርሲቲው በመከናወን ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ኦዲት ሲደረግ በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ የሚገኙ 11 ፕሮጀክቶች እንደሚገኙ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ዝርዝሩም፤

- በዋናው ግቢ የአስተዳደር ህንጻ ግንባታ ለማከናወን ከኤ.ኤል.ሲ. ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 27,908,796.60 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ 24/12/2008 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 98% መሆኑ፤
- በዋናው ግቢና ኦቶና ካምፓስ የሁለት መንትያ ክፍሎች ግንባታ ለማከናወን ከአበራ ልሳኑ ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 45,643,181.07 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ 01/05/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 98% መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ የሶስት መጋዘኖች ግንባታ ለማከናወን ከምንተስኖት አሰፋ ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 4,564,154.01 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ መስከረም 15/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 98% መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ የስታፍ ላውንጅ ግንባታ ለማከናወን ከልቡ ክፍሌ ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 5,277,566.66 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ

16/02/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 97% መሆኑ፤

- በዋናው ግቢ የAdditinal Water Work (bore hole) ግንባታ ለማከናወን ከደቡብ ውሃ ስራዎች ድርጅት ጋር የብር 9,244,223.69 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ 19/05/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 80% መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ የአበላ ምርምር ማዕከል ግንባታ ለማከናወን ከወንድወሰን አሰፋ ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 2,021,343.50 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ 24/01/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 80% መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ የአጥር ግንባታ ለማከናወን ከምንተስኖት ኦራጎ ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 1,268,703.00 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ 06/04/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 95% መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ የፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ዝርጋታ ሥራ ለማከናወን ከሳሙኤል ጌታቸው ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 2,344,447.50 የሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ 13/03/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ሥራው ያለበት ደረጃ 90% መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ የወጥ ቤት ግንባታ ለማከናወን ከታደሰ አደም ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 3,575,288.72 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ 24/09/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 70% መሆኑ፤
- በኦቶና ካምፓስ የላይብራሪ ግንባታ ለማከናወን ከአበራ ልሳኑ ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 24,399,265.38 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ 29/06/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 95% መሆኑ፤
- በተርጫ ካምፓስ የመማሪያ ክፍል ግንባታ ለማከናወን ከምሃስ ህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር የብር 10,629,835.20 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሰረት እስከ 05/13/2008 መጠናቀቅ ሲገባው ያልተጠናቀቀና ግንባታው ያለበት ደረጃ 95% መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.3.1.2 ስጋት ፣

የግንባታ ሥራዎች በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ካልተጠናቀቁ በታቀደው መሠረት ለአሠሪው መ/ቤት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ከመሆኑ ባሻገር ከግንባታ ዕቃዎች ዋጋ መጨመር አንፃር መንግስትን ላልተፈለገ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

2.3.1.3 **የማሻሻያ ሃሳብ** ፣

የግንባታ ሥራዎች በተገባው ውል መሠረት እንዲጠናቀቁ ተገቢ ቁጥጥር ማድረግና ሥራ በሚያጓትቱ የሥራ ተቋራጮች ላይ በወቅቱ ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

2.3.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ**፣

ግንባታዎቹ በተለያየ ምክንያት ያልተጠናቀቁ ሲሆን ከአማካሪና ከግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በኩል በሚደርሰን የመጨረሻ ክፍያ ላይ በውሉ መሠረት ተገቢው ይፈጸማል፡፡

2.3.2.1 **ግኝት፣ በወቅቱ ተመላሽ ያልተደረገ የግንባታ የቅድሚያ ክፍያ፣**

ዩኒቨርሲቲው እና የህንጻ ሥራ ተቋራጮች በገቡት የውል ስምምነት መሰረት ግንባታው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጮቹ የወሰዱትን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ ተመላሽ ማድረግ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት በግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በተሰጠን የግንባታዎች ያሉበት ደረጃ መረጃ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፤

- የደቡብ ውሃ ስራዎች በዋና ግቢና በኦቶና ሆስፒታል የውሃ ስራ ስራው ያለበት ደረጃ 80% ሆኖ ሳለ በውሉ መሰረት ግንባታው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጩ የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ መመለስ ሲኖርበት በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 05 ብር 508,183.18 ተመላሽ ያልሆነ ቅድሚያ ክፍያ የሚታይ መሆኑ፣
- ታደሰ ወንድወሰን በዋናው ግቢ የዶርሚተሪ ጥገና ስራው ያለበት ደረጃ 100% ሳለ በውሉ መሰረት ግንባታው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጩ የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ መመለስ ሲኖርበት በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 42 ብር 245,002.28 ተመላሽ ያልሆነ ቅድሚያ ክፍያ የሚታይ መሆኑ፣
- ልቡ ክፍሌ ህንጻ ስራ ተቋራጭ በዋናው ግቢ የስታፍ ላውንጅ ግንባታ ስራው ያለበት ደረጃ 97% በውሉ መሰረት ግንባታው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጩ የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ መመለስ ሲኖርበት በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 50 ብር 89,109.29 ተመላሽ ያልሆነ ቅድሚያ ክፍያ የሚታይ መሆኑ፣
- ምህረቱ ጌታሁን ህንጻ ስራ ተቋራጭ በዋናው ግቢ የላውንደሪ ቤት ግንባታ እና በኦቶና ካምፓስ የጥገና ስራ ስራው ያለበት ደረጃ 100% ሆኖ ሳለ በውሉ መሰረት ግንባታው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጩ የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ

ለሙሉ መመለስ ሲኖርበት በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 45 ብር 88,955.75 ተመላሽ ያልሆነ ቅድሚያ ክፍያ የሚታይ መሆኑ፣

- ሳሙኤል ጌታቸው ህንጻ ስራ ተቋራጭ በዋናው ግቢ የፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ዝርጋታ ስራ ስራው ያለበት ደረጃ 90% በውሉ መሰረት ስራው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጩ የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ መመለስ ሲኖርበት በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 66 ብር 313,701.39 ተመላሽ ያልሆነ ቅድሚያ ክፍያ የሚታይ መሆኑ፣
- ሼድ ህንጻ ስራ ተቋራጭ በዋናው ግቢ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ግንባታ ስራው ያለበት ደረጃ 99% በውሉ መሰረት ግንባታው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጩ የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ መመለስ ሲኖርበት በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 67 ብር 891,806.06 ተመላሽ ያልሆነ ቅድሚያ ክፍያ የሚታይ መሆኑ፣
- ምንተስኖት ኦራጎ ህንጻ ተቋራጭ በዋናው ግቢ የጀነሬተር ቤትና ሮቶ ማስቀመጫ እና የግቢ አጥር ግንባታ ስራው ያለበት ደረጃ 100% እና 95% እንደቅደም ተከተላቸው ሆኖ ሳለ በውሉ መሰረት ግንባታው 80% ሲሆነው ህንጻ ተቋራጩ የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ መመለስ ሲኖርበት በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 57 ብር 146,380.21 ተመላሽ ያልሆነ ቅድሚያ ክፍያ የሚታይ መሆኑ፣

በጠቅላላ ድምር ብር **2,283,138.16** የግንባታ ቅድሚያ ክፍያ በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ እና በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2.3.2.2 ስጋት፣

በግንባታዎቹ ሥራ መጓተት ለሌላ የልማት ሥራ ሊውል የሚችለውን ከፍተኛ መጠን ያለው የቅድሚያ ክፍያ በተቋራጮቹ እጅ እንዲቆይ እና ለሌላ ግንባታ እንዲያውሉት ዕድል ይሰጣል፡፡

2.3.2.3 **የማሻሻያ ሃሳብ** ፣

በውሉ በተቀመጠው መሰረት የግንባታው ደረጃ 80% ሲሆን ተቋራጩ የወሰደውን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ ለሙሉ መመለስ አለበት ፡፡ በመሆኑም አላግባብ በህንጻ ተቋራጮች እጅ ያለው ቅድሚያ ክፍያ ጊዜ ሳይሰጠው ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.3.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ከአማካሪ ማህንዲስና ከግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በኩል የመጨረሻ ክፍያ ሠርቲፍኬት ሲደርስ የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

2.4. የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሂሳብ አመዘጋገብን በተመለከተ፤

2.4.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ንዑስ ቁጥር 6 (ሀ) ማናቸውም የሂሳብ እንቅስቃሴ ያላቸው ሂሳቦች ሚኒስትሩ እውቅና በሰጣቸው የገቢ እና የወጪ ደረሰኝ መነሳት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ (ለ) የሂሳብ እንቅስቃሴ ያላቸው ሂሳቦች በእለት መዝገብ እና በሂሳብ ሌጀር መወራረስ እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡ (ሐ)በፋይናንስ ምንጫቸው የተመዘገቡ ከሂሳብ ሚዛናቸው ተወስዶ አመታዊ ሪፖርት መዘጋጀት እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል ሦስት የመንግስት የመ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ኃላፊነት አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1. መስሪያ ቤቱን በልዩ ልዩ ክፍሎችና ተግባራት እንደየባህሪያቸው ከፋፍሎ የማደራጀትና የውስጥ ቁጥጥርን መዘርጋት እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው ስር የሚገኘው የጤና ሳይንስ ህክምና ኮሌጅ፤

- የኮሌጁ ሂሣብ እንቅስቃሴ የተመዘገበው በፌደራል መንግስት የሂሳብ አመዘጋገብ (IBEX) ሳይሆን በማንዋል አሰራር መሆኑ፤
- የበጀት መቆጣጣሪያ፤ የገቢ፤ የተሰብሳቢ፤ የተከፋይ፤ የተጣራ ሀብት፤ የዝውውር፤ የመሳሰሉት በሌጀርና በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ /TR/ የማይመዘገቡ መሆኑ፤
- ኮሌጁ የሚጠቀምበት ሌጀርና የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ የፌደራል መንግስት ያዘጋጀው አለመሆኑና
- ኮሌጁ የሚጠቀምበት የሂሳብ ሌጀር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የማይዘጋና ቀጣይነት ያለው መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

2.4.2 ስጋት፣

- የሂሳብ እንቅስቃሴ ዘመናዊ በሆነ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ካልተያዘ ከፍተኛ ጊዜና ጉልበት የሚፈጅ ከመሆኑ በተጨማሪ ለስህተት የሚዳርግና ስህተቱንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈልጎ ለማግኘትም ሆነ ስህተትን ወዲያውኑ ለማስተካከል አያስችልም፡፡ እንዲሁም የውስጥና የውጭ ኦዲተሮች የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጊዜና ገንዘብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
- የኮሌጁ የሂሳብ አያያዝ በፌደራል መንግስት መመሪያ መሰረት ካልተመራ ለህገወጥ አሰራርና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

የኮሌጁ የመደበኛና የውስጥ ገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ ዘመናዊ በሆነ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) እንዲያዝ የስራ አመራሩ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ቀደም ሲል በባለሙያ እጥረት በማነ-ዋል የሂሳብ አመዘጋገብ እየሠራን የቆየን ቢሆንም በ2010 የበጀት ዘመን የIBEX ባለሙያ ስለተቀጠረ የተጠቀሱት የአሠራር ግድፈቶቹ የሚታረሙ መሆኑን እንገልጻለን።

3. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

3.1 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

3.1.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብ ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል። በዚሁ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በ4211 የሂሳብ መደብ ለተለያዩ እቃዎች መግዣ እና ውሎ አበል በቅድሚያ ክፍያ ወጪ ሆኖ በጊዜ ገደቡ ሳይወራረድ ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት የቆየ ብር 233,042.79 የሚገኝ መሆኑ፣
- በ4253 የሂሳብ መደብ ለተለያዩ ድርጅቶችና እቃ አቅራቢዎች ተሰጥቶ በወቅቱ ሳይወራረድ ከ1 ዓመት እስከ 3 ዓመት የቆየ ብር 9,443,260.60 የሚገኝ መሆኑ፣

በጠቅላላው ብር 9,676,303.39 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሣብ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል።

3.1.2 ስጋት፣

ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ካልተወራረዱ ከቆይታ ብዛት ወደ ማይሰበሰቡበት ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ።

3.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

በውዝፍ የሚታየው ተሰብሳቢ በወቅቱ እንዲወራረድ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል።

3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የተጠቀሱት ተሰብሳቢ ሂሣቦች እንዲወራረዱ እናደርጋለን።

4. በጀት

4.1 ግኝት፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል። የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 9,668,573.42 (24.14%) እና ከካፒታል በጀት ብር 82,882,473.10 (55.51%) ከዚህ ውስጥ ብር 11,221,074.47 በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ በመክፈቻ ሂሳብ የዞረ እና በተሰብሳቢ የተያዘ እንዲሁም በዚሁ በጀት ዓመት የተወራረደ ሂሳብ በመሆኑ ልዮነቱ ብር 71,661,398.63 በድምሩ ብር 81,329,972.05 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) በጀት ተገኝቷል።
- ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 1,543,667.59 (1.98%) እና ከካፒታል በጀት ብር 129,454,150.73 (28.03%) ከዚህ ውስጥ ብር 53,621,293.46 በበጀት ዓመቱ ለህንፃ ተቋራጮች በቅድሚያ የተከፈለ እና በተሰብሳቢ የተያዘ በመሆኑ ልዮነቱ ብር 75,832,857.27 በድምሩ ብር 77,376,524.86 ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል። ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር** 4 ቀርቧል።

4.2 ስጋት ፣

የተፈቀደው በጀት በዕቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ በሌሎች መ/ቤቶች ሊሰራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል። ከበጀት በላይ መጠቀም ተጠያቂነትን ያስከትላል።

4.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሰረት በስራ ላይ እንዲያውል፤ ከተፈቀደዉ በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የበጀት አጠቃቀም በተመለከተ በመደበኛና በካፒታል በጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ዙሪያ ጥንቃቄ እንድናደርግ የተሰጠውን የኦዲተር አስተያየት ተቀብለናል፡፡

5. ንብረት፣

5.1. የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ፣

5.1.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ንዑስ 5 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግሥት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤ የመጠቀም፤ የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ የሚል ሲሆን በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፤

የአላቂ እና የቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣

የዋናው ግቢ፣

- ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት ከትምህርት ሚኒስቴር በእርዳታ የገቡ በርካታ ዘመናዊ የምግብ ማብሰያ እቃዎች አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ መዝገቦች ከወጪቀሪ ጋር ያልተገናዘበ መሆኑ፤
- በቆጠራ ወቅት ብዛት ያላቸው አላቂ የሆኑ የግንባታ ዕቃዎች፣ የቢሮ ዕቃዎችና የትምህርት መሳሪያዎች ዋጋቸው ያልተገለጸ መሆኑ፤
- የቋሚ ዕቃ እና የአላቂ ዕቃ መጋዘን ጠባቂዎች በአዳዲስ ሰራተኞች ሲተኩ ርክክብ የተካሄደ ቢሆንም በውስጥ ኦዲት ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ፤
- የአላቂ ንብረት መጋዘን ንብረት የመያዝና የገቢና ወጪ ምዝገባ ሥራዎች በአንድ ሰራተኛ እየተከናወነ የሚገኝ መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ በርከት ያሉ አሮጌ ጎማዎች፣ የመኪና ባትሪ፣ ብላክ ቦርዶች፣ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፣ ሎከሮች፣ ፍራሾች፣ ትራሶች፣ ቆርቆሮዎች፣ የቀለም ቆርቆሮዎች፣ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ማይክሮስኮፖች፣ የኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያዎች፣ ቴሌቪዥኖች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖችና ስፒከሮች እንዲሁም ወንበርና ጠረጴዛዎች ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ የተቀመጡ መሆኑንና ክምችቱም እየጨመረ መምጣቱ፤
- በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የተማሪዎች መኖሪያ ህንጻ፣ የመማሪያ ህንጻና የአስተዳደር ቢሮዎች እንደ ቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ አለመመዝገባቸው፤

በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣

- በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ቋሚ፣ አላቂ እና አሮጌ እቃዎች ከንብረት ክፍል ጥበት የተነሳ በአንድ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የቋሚ፣ አላቂ እና የተመላሽ እቃዎች በአንድ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ንብረት የመያዝ እና ገቢ እና ወጪ የማድረግ ስራ የሚከናወን መሆኑ፤
- በንብረት ክፍል ውስጥ ቢንካርድ ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- የቋሚ ዕቃና የስቶክ መዛግብት ምዝገባ ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የንብረት ተጠቃሚ ሰራተኞች ካርድ (user card) ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- የንብረት ቆጠራ ስለመከናወኑ የሚገልጽ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- ለተማሪዎች ወርሃዊ፣ ሳምንታዊና ዕለታዊ የምግብ ግብዓት ከዋናው ግቢ የሚመጣ ቢሆንም ሞዴሎችና ቢንካርድ ሥራ ላይ ባለመዋሉ ገቢና ወጪ የሚከናወነው በደብዳቤ መሆኑ፣
- አራት የእንጀራ ምጣድ እና ስድስት ትላልቅ ድስቶች ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

5.1.2 **ስጋት፣**

- በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡
- በአሮጌ ዕቃዎች ላይ ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰዱ ለበለጠ ብልሽት እንዲዳረጉ ያደርጋል፤ የዕቃ ግምጃቤቱንም አላግባብ ያጣብባል፡፡
- ንብረት የመጠበቅ፣ገቢ እና ወጪ የማድረግ ስራ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን ከሆነ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

5.1.3 **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዲስተካከሉ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

5.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

በንብረት አያያዝና አጠባበቅ ዙሪያ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ለማስተካከል ጥረት እናደርጋለን፡፡

5.2. **የመድሃኒት አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ፣**

5.2.1 **ግኝት፣**

የፌዴራል ሆስፒታሎች የመደሀኒት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 001/2006 አንቀጽ 8.1 ከሆስፒታሉ የመድሃኒት መጋዘን ወደ ተለያዩ አገልግሎት መስጫ እና ማደያ

ክፍሎች አገልግሎት ወጪ የሚደረጉ መድሃኒቶች ክፍሎቹ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ የመድሃኒትና ህክምና ኮሚቴ ለየከፍሎቹ በሚዘጋጀው መዘርዝር መሰረት መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 9.1 ማንኛም ሆስፒታል መድሃኒት ለተጠቃሚው መሸጥ ያለበት ከ20% ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ ሲሆን የመድሃኒቶቹ ዋጋም በዝርዝርና በሚታይ መልኩ ለተጠቃሚው መለጠፍ እንዳለበት፤ እንዲሁም በክፍል አራት በአንቀጽ 19 ኦዲት ስለማስደረግ ማንኛውም ሆስፒታል በአጠቃላይ ሆስፒታሉ ውስጥ የሚከናወነውን የመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጥ አግባብነት የሆስፒታሉ የውስጥ ኦዲት መሪነት በመድኃኒትና ህክምና ኮሚቴ እና ጥራት ኮሚቴ የጋራ ትብብር ቢያንስ በየሩብ አመቱ ማስገምገም እንዳለበት፤ በአጠቃላይ በሆስፒታሉ ውስጥ የሚከናወነውን የመድኃኒት ቅብብሎሽ ስርዓቱን እና አገልግሎት አሰጣጡን ቢያንስ በበጀት ዓመቱ አንድ ጊዜ በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት በማስደረግ ለቦርዱ ማቅረብ እንደሚኖርበትና በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሆስፒታሉ በማንኛውም ጊዜ ኦዲት ማድረግ እንደሚችል ይገለጻል፡፡ በዚሁ መሰረት የሆስፒታሉ የመደሃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ከሆስፒታሉ የመድሃኒት መጋዘን ወደ ተለያዩ አገልግሎት መስጫ እና ማደያ ክፍሎች ከመሰራጨቱ በፊት ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ የመድሃኒትና ህክምና ኮሚቴ ለየከፍሎቹ በሚያዘጋጀው መዘርዝር መሰረት አለመሆኑ እና ይህ አሰራር በሆስፒታሉ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በሆስፒታሉ በዋናው የመድኃኒት መጋዘን ውስጥ በአንድ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ንብረት የመያዝ፣ ገቢ እና ወጪ የማድረግ ስራ እንደሚከናወን እንዲሁም ቢንካርድ፣ ስቶክ ካርድና ሞዴሎች ወቅታዊ ምዝገባ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የህክምና ቋሚ ዕቃ መጋዘን ቢንካርድ እና ስቶክ ካርድ የሌላቸው ሲሆን እቃዎችም በአግባቡ ያልተቀመጡ መሆኑ፤
- የመድኃኒት ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መጋዘን በአንድ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ንብረት የመያዝ እና ገቢ እና ወጪ የማድረግ ስራ እንደሚከናወንና ወቅታዊ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፤
- መድሃኒት ለተጠቃሚው መሸጥ ያለበት ከ20% ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ ሲሆን ሆሲፒታሉ 30% የትርፍ ምጣኔ በማድረግ መድሃኒት ለተጠቃሚው ከመሸጡ ባሻገር የመድሃኒቶቹ ዋጋም በዝርዝርና በሚታይ መልኩ ለተጠቃሚው ያልተለጠፈ መሆኑ፣
- ሆስፒታሉ የመድሃኒት ቆጠራ በሚያደርግበት ወቅት በቆጠራው ኮሚቴ ውስጥ የውስጥ ኦዲት በመሪነት መሳተፍ ቢኖርበትም በግቢው እንዳልተደረገ የቆጠራው ውጤት ከመድሃኒት መቆጣጠሪያ መዝገቦች ከወጪቀሪ ጋር የማገናዘብ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣

እንዲሁም ስቶክ ካርድና በቢን ካርድ ምንም ዓይነት ቆጠራ ስለመከናወኑ ማስረጃ የሚሆን ነገር አለመገኘቱ፤

- በሆስፒታሉ የመደኃኒት አቅርቦት፣ ክምችት፣ አያያዝ፣ አመዘጋገብ፣ ስርጭት፣ ሽያጭ እና አወጋገድ በሚመለከት ኦዲት አለመከናወኑ፤
- በስድስቱም የማደያ ክፍሎች የመድሃኒት ክምችት እና እንቅስቃሴን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ፣ ስቶክ ካርድ ወይም ዘመናዊ ሶፍትዌር በመጠቀም ያልተቆራረጠ ወቅታዊ ምዝገባ የማይደረግ መሆኑ፤
- የሆስፒታሉ የመድኃኒት ቆጠራ ኮሚቴ በሚቋቋምበትም ሆነ ቆጠራ በሚከናወንበት ወቅት የውስጥ ኦዲት ተሳትፎ እንዲኖረው አለመደረጉ፤
- ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች እስኪወገዱ ተለይተው እንዲቀመጡ የሚደረግ ቢሆንም ሳይወገዱ መቀመጣቸው፤ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

5.2.2 ስጋት ፣

- በመንግስት የወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ አለማድረግ ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡
- የመድሃኒት ቆጠራ ቢሚደረግበት ወቅት የቆጠራው ውጤት ከመድሃኒት መቆጣጠሪያ መዝገቦች ከወጪቀሪ ጋር የማይገናዘብ ከሆነ ቆጠራው የሆስፒታሉን ትክክለኛ የመደሃኒት አያያዝና አጠቃቀምን ላያሳይ ይችላል፡፡ እንዲሁም ቆጠራ ሲከናወን የውስጥ ኦዲት በዋነኝነት አለመሳተፍ የቁጥጥርና የማረጋገጥ ተግባር በአግባቡ ላይከናወን ይችላል፡፡
- በመድሃኒት ማደያ ክፍሎች ቢን ካርድ፣ ስቶክ ካርድ ወይም ዘመናዊ ሶፍትዌር በመጠቀም ያልተቆራረጠ ወቅታዊ ምዝገባ የማይደረግ ከሆነ የመደሃኒቶችን በቀላሉ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አያስችልም፡፡

5.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

- ከሆስፒታሉ የመድሃኒት መጋዘን ወደ ተለያዩ አገልግሎት መስጫ እና ማደያ ክፍሎች ከመሰራጨቱ በፊት ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ የመድሃኒትና ህክምና ኮሚቴ ለየክፍሎቹ በሚዘጋጀው መዘርዝር መሰረት መሆን ይኖርበታል፤ ይህ አሰራር በሆስፒታሉ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- መድሃኒት ለተጠቃሚው መሸጥ ያለበት ከ20% ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ በመሆኑ የትርፍ ምጣኔውን በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ በማድረግ የመድሃኒቶቹ ዋጋም በዝርዝርና በሚታይ መልኩ ለተጠቃሚው መለጠፍ ይኖርበታል፡፡
- የመድሃኒት ቆጠራ ቢደረግበት ወቅት የቆጠራው ውጤት ከመድሃኒት መቆጣጠሪያ መዝገቦች ከወጪቀሪ ጋር መገናዘብ ይኖርበታል፡፡

- በስድስቱም የማደያ ክፍሎች የመድሃኒት ክምችት እና እንቅስቃሴን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ፣ ስቶክ ካርድ ወይም ዘመናዊ ሶፍትዌር በመጠቀም ያልተቆራረጠ ወቅታዊ ምዝገባ ሊደረግ ይገባል፡፡

5.2.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ**፣

- ➢ የመድኃኒትና ህክምና ኮሚቴ ለየክፍሉ የመድኃኒት ዝርዝር አዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲያደርግ ይደረጋል፡፡
- ➢ በመመሪያው መሰረት 20% ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ ለመስራት በዝግጅት ላይ ነን፤
- ➢ የመድሐኒት ቆጠራ ውጤት ከመድኃኒት መቆጣጠሪያ መዝገቦች ከወጪቀሪ ጋር ያለመገናዘብ ችግር የሰራተኞች መዘናጋት ስለሆነ እናስተካክላለን፡፡
- ➢ ስድስቱም የማደያ ክፍሎች የመድኃኒት ክምችትና እንቅስቃሴ እየተደረገ ቢሆንም በዲሲፔንሰሪ ላይ ግን የቢን ካርድ አጠቃቀም ችግር የሚስተዋል በመሆኑ ይህንን ችግር በአፋጣኝ እናስተካክላለን፡፡ በመጨረሻም በኦዲተሮች የተነሱ እንደስጋት የታዩ ጉዳዮችን እኛም የለየናቸውና በአፋጣኝ የምናስተካክላቸው ጉዳዮች መሆናቸውን እንገልጻለን፡፡

5.3.1 **ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ**፣

5.3.1.1 **ግኝት**፣

የፌዴራል መንግሥት ተሽከርካሪዎች ሥምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል ሦስት አንቀጽ 9(2) እና (3) የተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታን በተመለከተ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንዳለበትና ለበላይ ኃላፊዎች ለመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሚውለው ነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት በተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በየወሩ ሪፖርት እንዲቀርብ በማድረግ ተገቢውን የአፈፃፀም ግምገማ መካሄድ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

5.3.1.2 **ስጋት** ፣

እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ ከሆነ የነዳጅ አጠቃቀሙን ለመከታተልም እና ለመቆጣጠር አያስችልም፡፡

5.3.1.3 **የማሻሻያ ሃሳብ** ፣

የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ለብክነትና ለምዝበራ እንዳይጋለጥ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር

እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ተገቢውን ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡

5.3.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

በ2009 በጀት ዓመት በጠቅላላ አገልግሎት ስር የሰራተኛ እጥረት ከመኖሩ የተነሳ በየወሩ ሪፖርት የሚሰራ (መረጃ ሰራተኛ) ባለመኖሩ ነበር፡፡ ለ2010 በጀት ዓመት የመረጃ ሰራተኛ በቅጥር ተጠይቆ ሂደት ላይ ስለሚገኝ በዚሁ ዓመት ማሻሻያ እናደርጋለን፡፡

5.3.2 **የጄነሬተር ነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ፣**

5.3.2.1 **ግኝት**

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል አራት ቁጥር 04(2) እያንዳንዱ መ/ቤት የሥራ ክፍል አንድን ሥራ ለመፈፀም ሥራው የሚያልፍበትን እያንዳንዱን ደረጃ በመዳሰስ ለሥራው ተስማሚና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት እንዲቀረጽ ማድረግ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሠረት ለጀኔሬተር የዋለ ነዳጅ ፍጆታ ኦዲት ሲደረግ፤

- በዋናው ግቢ እና በኦቶና ካምፓስ ለሚገኙ 8 ጀኔሬተሮች የነዳጅ ፍጆታ ሲዳሰስ ለጀኔሬተሮቹ የዋለውን የነዳጅ ፍጆታ ብዛትና የገንዘብ መጠን የሚገልጽ በማስረጃ የተደገፈ ሪፖርት ለማኔጅመንቱ ወይም ለሚመለከተው የስራ ሂደት የማይቀርብ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.3.2.2 **ስጋት**

ለጀኔሬተር አገልግሎት በሚውለው ነዳጅ ላይ አስተማማኝ የውስጥ ቁጥር ሥርዓት ካልተዘረጋ በከፍተኛ ገንዘብ የተገዛው ነዳጅ ለሚፈለገው ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አዳጋች ከመሆኑም በተጨማሪ ለብልሹ አሰራር መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

5.3.2.3 **የማሻሻያ ሃሳብ**

ለጀኔሬተር በሚውለው የነዳጅ ፍጆታ ላይ አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና የጀኔሬተሮች ነዳጅ አጠቃቀም ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ይገባል፡፡

5.3.2.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ**

ለጀኔሬተሮች ጥቅም ላይ የሚውለው ነዳጅ ሪፖርት እስካሁን ቀርቦ የማያውቅ በመሆኑ ክፍላችን አዲስ ተደራጅቶ ቀደም ሲል ይሰራ በነበረው አሰራር የቀጠለ ሲሆን ግኘ አፈጻጸም የነዳጅ አጠቃቀም መከታተያ ቅጽ እየተሞላ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱ ተገቢ መሆኑ ክፍላችን የተቀበለው ስለሆነ በተሰጠው አስታያየት መሰረት የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ለሚመለከታቸው የምናቀርብ መሆኑን እንገልጻለን፡፡ ከዚሁም ጋር ክፍላችን ስራውን የጀመረው በ2010 የበጀት ዓመት በመሆኑ

ከሐምሌ ጀምሮ በጥቅም ላይ የዋለው የነዳጅ ፍጆታ ሪፖርት በተገቢው መንገድ ተይዞና ተሰርቶ እንዲቀርብ የምናደርግ ይሆናል፡፡

6. ልዩ ልዩ፤

6.1. የውስጥ ገቢ ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ፤

6.1.1 ግኝት

የከፍተኛ ተምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ኦዲት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) በተደነገገው መሰረት የውስጥ ገቢን አጠቃቀም በተመለከተ እንደ አንድ መደበኛ አሰራር በየጊዜው ኦዲት ማድረግና አፈጻጸሙን ለተቋማቱ የበላይ ሀላፊ በየሩብ አመቱ ሪፖርት ማድረግ እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚሁ መሰረት የውስጥ ገቢ ሂሳብ በውስጥ ኦዲት የስራ ክፍል ኦዲት እየተደረገ በየሩብ አመቱ ለዩኒቨርስቲው የበላይ ሀላፊ ሪፖርት እንደሚደረግ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- የዩኒቨርስቲው የውስጥ ኦዲት ክፍል የውስጥ ገቢ ሂሣብን ኦዲት እያደረገ ሪፖርት የማያቀርብ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

6.1.2 ስጋት

የውስጥ ገቢ ሂሳብን በየጊዜው ኦዲት አለማድረግ የመንግስት ሀብትና ንብረት ለምዝበራ እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የዩኒቨርሲቲውን የውስጥ ገቢ ሂሳብ አጠቃቀምን በተመለከተ እንደ መደበኛ አሰራር በየጊዜው ኦዲት በማድረግ ለዩኒቨርሲቲው የበላይ ሀላፊ በየሩብ አመቱ ሪፖርት ማድረግ ይገባል፡፡

6.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ካለን የሰው ሃይል ማነስ የተነሳ የውስጥ ገቢ በሪፖርቱ መሰረት ለይተን ያላደረግን ሲሆን በኦዲት ስራችን ወቅት የተገኙ ግኝቶች ከመደበኛው ጋር በአንድነት የሪፖርት አካል የሆኑበት ሁኔታ ያለ መሆኑን እየገለጽን ለወደፊቱ በየሩብ ዓመቱ ከመደበኛ ሪፖርት ጋር የውስጥ ገቢንም የሰው ሃይል ከተጨመረልን እንደምንሰራ እንገልጻለን፡፡

6.2. የሰራተኛ ድልድልን በተመለከተ

6.2.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ምዕራፍ ሦስት አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 2 ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት አዲስ አደረጃጀት አጥንቶ ተግባራዊ ሲያደርግ ሠራተኞችን በማወዳደር ደልድሎ ማሠራት እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ በዚህ

መሠረት ኦዲት ሲደረግ በናሙና ከተመረጡት ሰነዶች መካከል በተቋሙ ፐሣ 9 የሥራ ደረጃዎች ላይ ያለውድድር (በሹመት) በመማር ማስተማር ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች፡-

1. መ/ር ያሬድ ከፍያለው በደብዳቤ ቁጥር ሠያ/1/1/1 በቀን 02/05/08 የህግ አገልግሎት ጽ/ቤት ዳይሬክተር፣
2. መ/ር ተሻለ ተገኔ በደብዳቤ ቁጥር ሠተ/1/1/6 በቀን 14/02/07 ኮሚዩኒኬሽንና ግብይት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣
3. መ/ርት አልማዝ ባልታ በደብዳቤ ቁጥር ሠአ/1/1/07 በቀን 27/04/09 የሥርዓተ-ፆታ ጽ/ቤት ዳይሬክተር፣
4. መ/ር አለማየሁ ኤልዳ በደብዳቤ ቁጥር ሠአ/1/1/4 በቀን 13/04/09 በተቋማዊ ለውጥ ጽ/ቤት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣
5. መ/ር መንግስቱ ጋልቾ በደብዳቤ ቁጥር ሠመ/1/1/07 በቀን 15/12/07 የሰው ሃይል ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣
6. መ/ር ኤፍሬም ገ/ሥላሴ በደብዳቤ ቁጥር ሠአ/1/1/09 በቀን 22/07/08 የቢዝነስ ልማትና ሃብት ማመንጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣
7. መ/ር አለማየሁ አሳሌ በደብዳቤ ቁጥር ወሶ/11/32/232 በቀን 22/07/08 የፐላንና ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፤ በመሆን ተመድበዋል፡፡

6.2.2 ስጋት

ከመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ውጭ ሠራተኛን መመደብ ፍትሐዊ ውድድር እንዳይኖር ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

6.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የሠራተኞች ምደባ ሲደረግ በአዋጁና መመሪያው መሠረት መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን ከላይ የተመለከተው የሠራተኞች ምደባ ጉዳይም ተጣርቶ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

6.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለቦታው የሚመጥኑ በቂ ባለሙያ ባለመኖሩ የተመደቡ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት አጠቃላይ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ እንደገና የቦታ ድልድል እየተሰራ ሲሆን ብቁ ተወዳዳሪዎች በቀረቡበት የምናስተካክል ይሆናል፡፡

6.3 የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይልን በተመለከተ

6.3.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፤ ዕውቀትና ክህሎት በላቸው ባለሙያዎች መደራጀት እንዳለበት ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት 9 የኦዲት ባለሙያዎች የሚያስፈልግ ሲሆን በአሁን ሠዓት 4 የኦዲት ባለሙያዎች ሲኖሩ ከዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይል መዋቅር ጋር ሲነፃፀር 5 የኦዲት ባለሙያዎች በቅጥር ያልተሟሉ መሆኑ፤ በዚህም ምክንያት የ2ኛ ሩብ ዓመት ኦዲት ሪፖርት በወቅቱ ሳይቀርብ ከ3ኛ ሩብ ዓመት ኦዲት ሪፖርት ጋር የቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

6.3.2 ስጋት

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ተገቢው የሙያ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች ካልተደራጀ በዩኒቨርሲቲው የተዘረጋውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ጠንካራና ደካማ ጎኑን በመለየት ለዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር በተገቢው መንገድ ሳይቀርብ ይችላል፡፡

6.3.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል የሚጠበቅበትን አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የሰው ኃይሉ ተገቢው የሙያ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲሟላ ተገቢው ጥረት እንዲደረግ እና ባለው የሰው ኃይል ሊሰራ የሚችለውን ሥራ በወቅቱ እየሰራ እንዲያቀርብ መከታተል ይገባል፡፡

6.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከዚህ በፊት ማስታወቂያ ወጥቶ መስፈርቱን የሚያሟሉ ተወዳዳሪዎች ባለመቅረባቸው ሳይሟላ የቀረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት የመምሪያው ስራ ተጠሪነቱ ለገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር በመሆኑ ከጥር 2009 ዓ.ም ጀምሮ ያልተሟሉ ሰራተኞች በሚኒስተር መ/ቤቱ እንደሚሟላልን በመገለጹ በአሁኑ ጊዜ ምልሻቸውን እየተጠባበቅን እንገኛለን፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!

አባሪ ቁጥር 1. ለአስተዳደር ሰራተኞች የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ

ተ.ቁ	ቀን	የደረሰኝ አይነት	የደርሰኝ ቁጥር	የሂሳብ መድብ	የተከፈለበት ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	11/07/09	JV	284657	6116	በምድረ-ግቢ ደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ስር ለሚገኙ ሰራተኞች ትርፍ ሰአት ክፍያ	29,831.40
2	16/02/09	JV	938345	6116	በምድረ-ግቢ ደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ስር ለሚገኙ ሰራተኞች ትርፍ ሰአት ክፍያ	97,945.51
3	13/01/09	JV	938624	6116	በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ስር ለሚገኙ ሰራተኞች ትርፍ ሰአት ክፍያ	34,992.80
4	27/12/08	JV	938219	6116	በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ስር ለሚገኙ ሰራተኞች ትርፍ ሰአት ክፍያ	26,275.20
5	20/03/09	JV	938728	61□6	በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ስር ለሚገኙ ሰራተኞች ትርፍ ሰአት ክፍያ	34,094.24
6	12/03/09	JV	938358	6116	በምድረ-ግቢ ደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ስር ለሚገኙ ሰራተኞች ትርፍ ሰአት ክፍያ	90,805.01
7	02/09/09	JV	194924	6116	በምድረ-ግቢ ደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት ስር ለሚገኙ ሰራተኞች ትርፍ ሰአት ክፍያ	37,434.19
					ድምር	**351,378.35**

አባሪ ቁጥር 2. ተቆራርጦ በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸሙ ግዥዎች (ዋናው ግቢ)

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	አቅራቢው ድርጅት	የወጪው ምክንያት	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	19/10/09	BPV 282943	ዛክ ማተሚያ	የመጽሐፍት ሕትመት	6215	134,895.00
2	22/05/09	BPV 282870	ማርታ የጽፈት መሳሪያ መደብር	ፕሪንተር ወረቀት፣ ደብተርና እስክሪፕቶ (የጽፈት መሳሪያ)	6212	88,652.35
3	24/05/09	JV 938065	ራንቺም ኢ.ዲስትሪና ንግድ፣	የጽፈት መሳሪያ	6215	199,500.39
				የእንጀራ ምጣድ ምድጃ	6218	33,000.00
4	27/08/09	JV 938092	አሚና አብዱላሂ አህመድ	የወፍጮ መለዋወጫ ዕቃዎች	6218	113,441.09
5	28/10/09	JV 284569	ቴዲ ባህላዊና ዘመናዊ አልባሳት እና ትራንስፖርት	የእስከርቭ ግዥ	6211	71,760.00
6	27/10/09	JV 68897	እናት ህትመትና ማስታወቂያ ሥራ	ህትመት ግዥ	6213	82,800.00
7	26/11/08	BPV 239023	ከእናት ህትመትና ማስታወቂያ እና ከነዓን ህትመት ስራ	ህትመት ግዥ	6213	53,902.80
8	09/03/09	BPV 241206	ጌታብጽገሕ ፋሚሊ አጠቃላይ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማ	የህትመት ግዥ	6215	199,999.80
9	14/09/09	BPV 242826	ፕሮፌሽናል ዘመናዊ ልብስ ስፌትና ጨርቃ ጨርቅ መደብር	ቦርሳ ከአብጀዲ የተሰራ	6218	144,900.00
					ድምር	977,951.43

አባሪ ቁጥር 3. ተቆራርጦ በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸሙ ግዥዎች (ኦቶና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ)

ተ.ቁ	ቀን	የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ	አቅራቢው ድርጅት	የወጪው ምክንያት	የሂሳብ መደብ	የገንዘብ መጠን
1	30/03/09	JV.466648	የተለያዩ አቅራቢዎች	ለጥገና አገልግሎት	6244	93,492.10
2	30/09/09	JV.150765	የተለያዩ አቅራቢዎች	ለመኪና ጌጣጌጥ	6241	93,552.50
3	30/05/09	JV.150753	የተለያዩ አቅራቢዎች	ለግንባታ ጥገና አገልግሎት የሚውሉ	6244	103,729.23
4	30/05/09	JV.150753	የተለያዩ አቅራቢዎች	ለላብራቶሪ ማሽን ጥገና እና የህክምና መሳሪያዎች ጥገና	6243	150,700.00
5	30/10/09	JV.150770	የተለያዩ አቅራቢዎች	ለተለያዩ ፈርኒቸሮች ግዥ	6313	760,777.50
6	30/10/09	JV.150770	ያሲን ከማል ሱፐር ማርኬት	አላቂ የጽዳት ዕቃዎች ግዥ	6218	63,665.00
7	30/10/09	JV.150770	ህልፉ የጽፈት መሳሪያ	የጽፈት መሳሪያ ግዥ	6212	32,800.02
8	30/10/09	JV.150770	ናቲ የጽፈት መሳሪያ	የጽፈት መሳሪያ ግዥ	6212	31,400.75
9	30/10/09	JV.150770	ህልፉ የጽፈት መሳሪያ	የጽፈት መሳሪያ ግዥ	6212	57,988.75
10	30/05/09	JV.150770	ከነሐን ማተሚያ ቤት	ለህሙማን ካርድ ግዥ	6213	199,670.00
11	30/04/09	JV 150751	የተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች	ለጥገና አገልግሎት (የተለያዩ ግንባታ ዕቃ ግዥ)	6244	154,415.20
12	30/10/09	JV 150770	የተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች	ለህክምና መሳሪያዎች ጥገና	6243	184,538.50
13	30/10/09	JV 150770	ሲሳይ ልብስ ስፌት	የደንብ ልብስ ግዥ	6211	151,196.15
14	30/10/09	JV 150770	ያህዌንስ ጨርቃ ጨርቅ	የደንብ ልብስ ግዥ	6211	19,808.75
15	30/10/09	JV.150770	ሲሳይ ልብስ ስፌት	የተማሪዎች ጋዋን የተሰፋበት	6211	35,315.00
ድምር						2,133,049.45

አባሪ ቁጥር 4. የ2009 በጀት ዓመት የበጀት ማመዛዘኛ

የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ስራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት በጀት	%
	ያልተሰራበት በጀት (መደበኛ)			
6212	5,370,000.00	4,760,612.81	609,387.19	11.35%
6215	6,000,000.00	3,076,170.64	2,923,829.36	48.73%
6218	5,370,300.00	3,806,221.99	1,564,078.01	29.13%
6221	331,300.00	282,547.26	48,752.74	14.72%
6222	100,000.00	87,973.31	12,026.69	12.03%
6223	5,240,700.00	4,313,233.32	927,466.68	17.70%
6232	2,905,000.00	2,410,633.73	494,366.27	17.02%
6251	1,105,200.00	842,575.32	262,624.68	23.76%
6253	1,200,000.00	1,019,527.08	180,472.92	15.04%
6255	920,900.00	617,456.73	303,443.27	32.95%
6256	550,900.00	430,649.24	120,250.76	21.82%
6257	693,575.00	363,067.09	330,507.91	47.65%
6258	6,700,000.00	5,654,337.31	1,045,662.69	15.61%
6259	567,750.00	121,258.19	446,491.81	78.64%
6417	3,000,000.00	2,600,787.56	399,212.44	13.31%
ድምር	**40,055,625.00**	**30,387,051.58**	**9,668,573.42**	**24.14%**
	ያልተሰራበት በጀት (ካፒታል)			
6313	72,712,767.00	15,057,256.37	57,655,510.63	79.29%
6314	50,308,900.00	41,349,716.96	8,959,183.04	17.81%
6321	22,900.00	-	22,900.00	100%
6324	26,261,153.00	10,016,273.57	16,244,879.43	61.86%
ድምር	**149,305,720.00**	**66,423,246.90**	**82,882,473.10**	**55.51%**
የሂሳብ መደብ	**ስራ ላይ የዋለ**	**የተስተካከለ በጀት**	**ከበጀት በላይ የወጣ**	**%**
	ከበጀት በላይ የወጣ (መደበኛ)			
6114	5,033,639.00	4,945,000.00	88,639.00	1.79%
6116	13,002,112.64	12,729,920.00	272,192.64	2.14%
6121	19,137,562.70	18,683,333.00	454,229.70	2.43%
6211	4,906,756.36	4,600,600.00	306,156.36	6.66%
6231	19,499,411.62	19,370,667.00	128,744.62	0.67%
6241	12,135,915.78	12,085,151.00	50,764.78	0.42%
6243	1,564,139.59	1,530,300.00	33,839.59	2.21%
6244	3,138,904.81	2,983,900.00	155,004.81	5.20%
6254	1,252,496.09	1,198,400.00	54,096.09	4.51%
ድምር	**79,670,938.59**	**78,127,271.00**	**1,543,667.59**	**1.98%**
	ከበጀት በላይ የወጣ (ካፒታል)			
6115	42,314,183.63	42,059,139.00	255,044.63	0.61%
6124	5,345,925.88	5,299,377.00	46,548.88	0.88%
6232	1,007,182.00	802,400.00	204,782.00	25.52%
6322	35,119,310.11	32,000,000.00	3,119,310.11	9.75%
6323	503,033,625.92	377,205,160.81	125,828,465.11	33.36%
ድምር	**586,820,227.54**	**457,366,076.81**	**129,454,150.73**	**28.30%**